ከገብሩ አድጋቦ ሕዳር 27-2000

ቬነስ - ጣሊያን

# «የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ!»

(መታሰቢያነቱ በትግራይ «ጉአንታናሞ» በእስር ለሚማቅቁ ለፀጋዬ ገ/መድህን፤አበራሽ በርታ፤ይስሐቅ፤በለጠ ለሌሎቹም ይሁን)

«ፊርማ ዕና ወረቀት፤ ጠፊ ነው ተቀዳጅ

መተማማን በቻ፤ይበቃል ለወዳጅ»

ይሄ ነበር የጥንት ወጉ

መሰረቱ፤የሀቅ ጥጉ

ዕምነት ደርዙና ማዕረጉ

መቃን-ጉበን፤ፍርግርጉ

ዙሪያ ግድግዳ፤ምርጉ

ማሕተቡ ዕና ፊለጉ

አልነበረም፤አረግርጉ

የዕምነት ጠገጉ

ያወረሱን፤ደጋጉ::

«ገና-ለገና፤ተመታ-በገና!»

አዲሱ ቀኖና

ለወያኔ ዕውቅና

ዘመን ተለዋወጠና

ተደስኩሮ ምንሚና

ተቆጥሮ፤ከስልጠና

ነውር ሙልጭ ተደረገና

መለኪያው የሰብዕና

ወግ-ማዕረግ፤ወለቀና

ተለበሰ ገበና

ንዋይ ከበረና

በ ወገን ለይ ድገና

ዓይን ዕያየ ምከና

በ አገር ላይ ሸርሙጥና

ወደ ሲያል፤ምነና

ሥይጠና! ሥይጠና!

የዕለፍ-ዓመቱ «ሆይ ሙና!»፡፡

ቃል!፤ማሕተብ፤ቃል!

የዕምነት ኪዳን፤ውል

የክብረት ሚዛን፤ጠለል

የጀግንነት ቅዱስ ጠበል፡፡

## ሆነና! «የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ?!»

ጋሻቸው መዘዝ መዞ

ከካናዳ-አትላንታ፤ጠልዞ

የብተና ዶሴ ጠርዞ

የሆድን በሆድ ይዞ

ቂምና ክፋት ዐርግዞ

ተመሳስሎ ተወዛውዞ

ሐቅና ሽፍጥ በርዞ

አስመስሎ ለሩቅ ጉዞ

ወንድምን በቁም ቀብሮ

ሽ ፍ ኖ!፤ከ ፍ ኖ!፤ገ ን ዞ!

ከአንገት በላይ፤ብሎ አይዞ

በሆድ አኬት አርግዞ

በጥቅም ፈዞ፤ነፍዞ

ገድል በርዞ፤ደልዞ

ደግሞ ያነባል፤ዕንደ አዞ::

## ሆነና! «የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ?!»

ቀድሞ ቢታወቅማ

“የመሃንዲሱ” ዕድማ

“የታዳጊ-ነኙ!” ጀማ

የካናዳው አውድማ

የኦቶዋው ጂኒማ

ዋ! ቢታወቅማ

ለወያኔ ማርገዱ

የሕዳጣን ፧ሸርጉዱ

የክህደት፧ጉድጉዱ

ሆነና! «የሰው ሆዱ፧የወፍ ወንዱ?!»

ያቂመው ጉ-ዳ-ጉ-ዱ

በዕምነት በመጋረዱ

ለፍቅር በመገደዱ

ቢዘገይም ለየ ጉዱ!

ትግል በቃኝ አንድ ነው

ጡረታም የአባት ነው

በመጨረሻ በመጦሪያው

ገድል በመቋጠሪያው

ለስልጣን አንጠራራው

ለአንጅንት ግርሻ

ለንዲህ ዐይነቱ ቁሻሻ

የወንድሜ ዝናር. . .

. . . ነበረ ማርከሻ!

ለከሃዲ መርሻ፡፡

<u>ሆነና! «የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ?!»</u>

እጅግ ያስቸግራል

ያለሰው ይኖሯል?

ዕንቅልፍ ተፈርቶ፤

ቆሞ ይታደራል?

ከሃዲ ተፈርቶ

ከትግል ይሸሿል?

የአንጅነትን፤ክህደት

"ዕሳት ካየው፤ምን ለየው?"

<u>ወያኔ ወያኔ ነው</u>

<u>አንጃም ከሃዲ ነው</u>

ከሃዲም አንጃ ነው

ዕርቃኑን ያሰቀሯል

አይቀጡ፤ይቀጡአል

ግብግብ ይገጥሟል

ማንቁርቱን ይይዟል

ይወድቋል፤ይነሷል

ይጥሏል፤ይረቷል

“በግ ከበረረ፤ነገር ከከረረ”

ወደ ሁዋላ አይመለስ

ወያኔን ከሃዲን፤

ባንድ ላይ ነው ማጥቀስ

ደማምሮ ማስነጠስ

የምን መለሳለስ?!

ለጥፋት መሐንዲስ!

ደግሞ ለግብስበስ!!

የውቂያኖስ ጥልቀት

የሰማይን ስፋት

የክዋክብትን ርቀት

ጫፍ የሌለው ግዝፈት

በሜትር አይለኩት

በኪሎ አይመዝኑት

በጣሳ አይሰፈሩት

በመጫኛ አያስሩት

አደራ የሰማእት

መሀላ በሕይወት

አቻም አይወጣለት፡፡

ግን ሆነና!«የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ!»

አድብተው፤ነገዱ

እጅጉን ቀለዱ

በታኞች ተራዱ

አበዱ፤አረገዱ!

ውሉን ቀዳዱ

ሸኑና፤ሰገዱ፡፡

«የሰው ሆዱ፤የወፍ ወንዱ!» ቸር ይግጠመን